**የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ አባሎቹን በማብጠልጠሉ ከፍተኛ ትችት እደረሰበት ነው፤**

**የብአዴን እና የህወሀት ችግር እየሰፋ መሆኑ ተነገረ፤**

**ወያኔ ለልመና የላከው ቡድን በኪሳራ ተመለሰ፤**

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ማክሰኞ ሚያዚያ 5 ቀን 2002 ዓ ም. ለተወካዮች ምክር ቤት ባቀረበው ሪፖርቱና በሰጠው ማብራሪያ ላይ አባሎቹና ባለስልጣናቱ ከፍተኛ ትችት እየሰነዘሩበት መሆኑ ታወቀ::

በዚሁ ባቀረበው የዘጠኝ ወር ሪፖርት ላይ እንደጠቀሰው ከሆነ ሀገሪቱ ከአፍሪካ ግንባር ቀደም በመሆን እድገት እያስመዘገበች ትገኛለች ቢልም የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች በተለይ እነ አቶ ቡልቻ ደመቅሳ ግን እድገቱ የሚታይ አይደለም...... የተባለውም እድገት ፍፁም ውሸት እና ጉንጭ አልፋ ብቻ ነው በማለት ክፉኛ የተቹት መሆኑም ታውቆዋል::

አጉራ ዘለል በሆነው ባህሪው እንደ ልቡ እየተሳደበና እየተዛለፈ ባሳለፈበት በዚሁ ሪፖርቱ ላይ የተቃዋሚ መሪዎቸ የቀረበውን ሪፖርት በማጣጣላቸው እና በማብጠልጠላቸው እጅግ በመበሳጨት ስድብ አዘል ምላሽ የሰጣቸው ከመሆኑም በላይ ዛቻ እና ማስፈራሪያ እንደሰነዘረባቸው በቀጥታ ከተላለፈው ራዲዮና ቲሌቪዥን ለመረዳት ተችሎዋል::

ዶክተር መረራ ጉዲና በበኩላቸው ዘንድሮ ሊደረግ ጥቂት ቀናት በቀረው ምርጫ ዙሪያ ወያኔ እራሱን ብቻ ለማስመረጥ በህዝቡ ላይ የሚያደርሰውን ጫና ካላስወገደ አደገኛ ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል ከወዲሁ ብታስተካክሉት ይሻላል የሚል ሀሳብ የሰነዘሩ ቢሆንም የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ግን በብስጭት እና በንዴት ጠረጴዛ እየደለቀና ውሀውን አሁንም አሁንም እየተጎነጨ ሁለት ቦታ እየረገጡ መጉዋዝ ጊዜው ያለፈበት በመሆኑ ሀሳቡም መነሳት የለበትም በማለት ማስፈራሪያ መስጠቱ ታውቆዋል::

እብሪተኛው የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ አክሎም በአሁኑ ሰዓት ሊደረግ በተቃረበው ምርጫ ሊበጠብጥ የሚሞክር ካለና ያሰበ ቢኖር እጁ ይቆረጣል ምላሱ ይበጠሳል በማለትም መስፈራራቱ ተደምጦዋል::

በዕለቱ ከወትሮው በተለየ መልኩ የወያኔ አፈድፋጅ የሆነው ልደቱ አያሌውን በምስጋና ሲንያበሽብሸው የዋለው መለስ ከዚህ ቀደም በሰላማዊ ትግሉ ከጎናችን ሆነው እንደሰሩት ሁሉ ወደፊትም እንዲገፉበት እንሻለን.......አደራ እንዳይንሸራተቱብን በማለትም ተማፅኖ አቅርቦለታል::

አቶ ልደቱ በሚወዳደርበት ሳሊበላ ቡግና ወረዳ ከዞን እስከ ወረዳ ብሎም እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉት የብአዴን ካድሬዎች የተቃዋሚ እጩዎችን ሀይማኖት የለሾች ናቸው እያሉ ለህዝቡ እየቀሰቀሱ ነው በሚል ልደቱ ባቀረበው አቤቱታ መሰረት እብሪተኛው መለስ ሙልጭ አድርጎ የራሱን አባሎች መሳደቡንም ቀጥታ በተላለፈው ስርጭት ለመረዳት ተችሎዋል::

በዚሁ ምላሹ ላይ እንዳለው ከሆነ ከወትሮው በተለየ እና እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ የብአዴን ካድሬዎችን ወራዳ...... የወራዶች ወራዳ...... ሌባ...... በማለት እየደጋገመ ከመሳደቡም ሌላ እንደጭቃ ሲያልኮሰኩሳቸው ተደምጦዋል::

ከዚህ ቀደም በህወሀት እና በብአዴን መሀከል ከፍተኛ ክፍተት ተፈጥሮ እንደነበር መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን ሰሞኑንም መለስ ዜናዊ የሰጠው ምላሽ ከዚሁ ግጭት እና ንትርክ ጋር ተያይዞ ሳይሆን እንዳልቀረና የብአዴኖችን አንገት ለማስደፋት ሆን ብሎ የወሰደው እርምጃ ሊሆን እንደሚችል የፖለቲካ ተንታኞች ሲናገሩ ተደምጦዋል::

በተለይ የወያኔ ነባር እና አዳዲስ አባሎች በመለስ መልስ እጅግ የተበሳጩ ከመሆኑም በላይ በአደባባይ በየመሸታ ቤቱ ሲሳደቡና ሲያመናጭቁት የተደመጡ ሲሆን ችግር እንኳዋን አድርሰዋል ቢባል በውስጥ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በተዋረድ መቅጣት እና እርምጃ መውሰድ ሲቻል በግልጽ በይፋ እያንቋሸሸ መሳደቡ አምባገነን መሆኑን በግልጽ ያሳየበት ነው ሲሉም የራሱ ካድሬዎች በብስጭት ሲሳደቡ ተደምጠዋል::

ሆድ በባሳቸው እና ውስጣቸው ቂም ቁዋጥሮና አርግዞ ባለበት በዚህ ወቅት መለስ ዜናዊ በድፍረት እና በማን አለብኝነት የራሱን አባሎች ሙልጭ አድርጎ ማብጠልጠሉ ሳያንስ እጅ እቆርጣለሁ....... ምላስ እቀነጥባለሁ....... እያለ ማስፈራሪያ በመሰንዘሩም በተለይ አዲስ አበባ ያሉት የብአዴን አባላት ከመጠን በላይ ከመበሳጨታቸው የተነሳ መለስን በየቦታው በግልጽ ማማት መጀመራቸው የወያኔ የመጨረሻው መጀመሪያ መሆኑን ያሳየ ነው የሚሉም ወገኖች በርካቶች ናቸው::

ባሳለፍነው ወር መጀመሪያ ላይ የወያኔ አሰቸኩዋይ ስብሰባ በተደረገበት ወቅት በሚቀጥሉት ወራት ውስጥ ከምርጫ በሁዋላ ከወያኔ የሚሰናበቱትን እና የሚሾሙትን

በሙሉ ስልጣኑ እንዲያከናውን ለመለስ ዜናዊ ያፀደቀለት በመሆኑ በእብሪት እና በትዕቢት ልቡ በመደፈኑ የራሴ ናቸው የሚላቸውን ሁሉ ማብጠልጠል መጀመሩ አምባገነንነቱ ይበልጥ አፍጥጦ እና አግጥጦ መውጣቱን ያሳየ መሆኑን ካድሬዎቹ እየገለፁ ናቸው::

በፍርሀት እና በጭንቀት ውስጥ የወደቀው ይሄው የወያኔ ቡድን የራሱን አባሎች እና ሹማምንቶች ጭምር ባለማመኑ በየቀኑ ስብሰባ እየጠራ ስለ ምርጫው ቢጎተጉታቸውም አባላቱ የበለጠ እየሰለቹ በመምጣታቸው ከስብሰባ መቅረት መጀመራቸውም ታውቆዋል::

በሌላ በኩል የአማራ ልማት ማህበር የተባለው የወያኔ ተለጣፊ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ድርጅት ከቀድሞው አባሎቹ እና ከህዝቡ በግዴታ በተዋጣ ገንዘብ ብዛት ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ እርስ በርስ ሽኩቻ መጀመሩን የውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋለጡ::

በወያኔ ባለስልጣናት መሀከል የተነሳው ፀብ በህወሀት እና በብአዴን ውስጥ መሆኑን የጠቆሙት የውስጥ አዋቂ ምንጮች የአማራ ልማት ማህበር (አልማ) የተባለው የወያኔ ማህበር በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ከህዝቡ በግዴታ .....ከአባሉ በማስፈራራት......ከዲያስፖራው ሀገርህ መግቢያ በሚል በተጭበረበረ መንገድ ተግበስብሶ የተገኘ ገንዘብ መሆኑን እያወቁ የጋራ መሆን አለበት እንጂ ብአዴን ብቻውን ሊያፍስ አይችልም በሚል የተጀመረ ሽኩቻ መሆኑንም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል::

የአማራን ህዝብ ለወያኔ አሳልፎ የሰጠ እና በችግር እና በችጋር እግር ከወርች ታስሮ የሚገኘውን ህዝብ እወክላለሁ በሚል ሰንካላ እና ቁንፅል ሀሳብ የተመሰረተው የአማራ ልማት ማህበር በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እያሰባሰበ በመገኘቱ ገንዘቡ የጋራ እንጂ የግል ሊሆን አይችልም በማለት የህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣናት እና ካድሬዎች ጥያቄ ቢያቀርቡም የብአዴኑ ተወካይ ህላዊ ዮሴፍ ግን ደክመን እና ለፍተን ያመጣነው ገንዘብ በመሆኑ የግላችን ......የድርጅታችን ነው በማለት ምላሽ በመስጠቱ ተለኩሶ የነበረው ውዝግብ እንደተባባሰ ምንጮቹ አስረድተዋል::

በህወሀት እና በብአዴን መሀከል የተጀመረው ክፍፍል እየሰፋ እና እየለየለት የመጣው ዛሬ አይደለም ያሉት የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ በተለይ መለስ ስልጣኑን ሙሉ በሙሉ ከጠቀለለ ወዲህ እና ህወሀት በሀገሪቱ ከቀበሌ እስከ ዞን ድረስ ተስፋፍቶ ስልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን አስታውሰው አንዳንድ የብአዴን ወጣት እና ነባር ካድሬዎች በዚሁ ድርጊት በመበሳጨታቸው በወያኔ ላይ ከፍተኛ ውግዘት ማድረስ በመጀመራቸው መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ምንጮቹ እንዳሉት ይበልጥ ፀቡን ያከረረው ህላዊ ዮሴፍ ከዚህ ቀደም በአደባባይ እኛ የበላይ ነን ወደፊትም እኛው ብሎ በመናገሩ እንደሆነ የጠቆሙት ምንጮቹ አሁንም በድጋሚ የሄንኑ በማለቱ ስፊ ውዝግብ ውስጥ መግባታቸውን አክለው ገልፀዋል።

በብአዴን እና በህወሀት ከፍተኛ ካድሬዎቹ የተጀመረው ሽኩቻ እና ንትርክ ውስጥ ውስጡን ስር እየሰደደ መጥቶ ዛሬ ላይ ሊፈነዳ በሚችልበት ደረጃ ላይ መድሱን ምንጮቹ ጠቁመው መለስም ይሄንኑ ተከትሎ ለልደቱ ወግና በምክር ቤት ብአዴኖችን ሙልጭ አድርጎ መሳደቡ እጅግ ነገሩን ሊያከርረው እንደሚችል ምንጮቹ ስጋታቸውን ገልፀዋል።

በውስጥ እና በውጭ ግፊት ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ የገባው የወያኔ ቡድን ጊዜያዊ ማስተንፈሻ ይሆነኛል በሚል አዲስ ዘመቻ መጀመሩ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቢሮ ሾልኮ የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል።

የወያኔ ቡድን ባጋጠመው ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሳራ መጠገኛ እንዲሆነው በአውሮፓ የተለያዩ ሀገራት እየተዘዋወረ ልመና የሚያቀርብ በወያኔው ቁንጮ ባለስልጣን ስዩም መስፍን መሪነት አንድ ልዑካን ቡድን የላከ ቢሆንም ቡድኑ የተላከበትን አላማ በበቂ ሁኔታ ሳያሳካ መመለሱን ምንጮቹ ጠቁመዋል።

በስዩም መስፍን የሚመራው ይሄው የወያኔ ልዑካን ቡድን በጣሊያን፣በፊንላንድ እና በኖርዌይ በመዘዋወር የገንዘብ እርዳታና ብድር ብሎም የፖለቲካ ድጋፍ እንዲያደርጉለት በየሄደበት ጥያቄ ቢያቀርብም የተለያዩ ምክንያቶችን እየደረደሩ መንግስታቱ ጥያቄውን ውድቅ አድርገውበት በሀፍረት መመለሱን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አብራርቶዋል።

ሁለት ዓለማን አንግቦ ወደ አውሮፓ የተጉዋዘው ይሄው የወያኔ ቡድን በሀገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ እድገት አስመዝግቤያለሁኝ ለዚህ ጅማሮ ወደፊት በይበልጥ እንድንጉዋዝ ይረዳኝ ዘንድ የገንዘብ ድጋፍ ይደረግልኝ አሊያም ብድር ይሰጠኝ በማለት ለተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት ቢያቀርብም የአውሮፓ ሀገራት መሪዎች ወቅቱ አሁን እንዳልፈቀደላቸው እና ጉዳዩን እንደሚያስቡበት በመግለፅ እንዳሰናበቱት ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ሌላው ሁለተኛው የወያኔ የልዑካን ቡድን ተልእኮ የፖለቲካ ድጋፍ እንዲደረግለት እና በተለይ በመጪው ምርጫ ጥራቱን የጠበቀ ምርጫ ስለማደርግ እውቅና ይሰጠኝ ቢልም የ1997 ዓ.ም ጅማሮ ጥሩ ቢሆንም አጨራረሱ ያላማረ በመሆኑ በአሁኑ ሰዓት ማረጋገጫ ስለሌለን ድጋፍ መስጠቱ ይከብደናል በሚል አዋርደውና አንኩዋስሰው ብሎም አበሳጭተው ቡድኑ በኪሳራ ሊመለስ እንደቻለ ምንጮቹ አስረድተዋል።

በሀገር ውስጥም ያሉትን የአውሮፓ ሀገራት አምባሳደሮች በተለያዩ ትላልቅ ሆቲሎች እራት እየጋበዙ እየተለማመጡ ቢሆንም እነሱም እንደ መሪውቹ እናስብበታለን በማለት ምላሽ በመስጠታቸው ወያኔ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ኪሳራ ውስጥ መውደቁን ለዲፕሎማቶች ቅርበት ያላቸው ወገኖች ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

ክፉ ጊዜ ሲያገኙ የሚያሽቀነጥሩት......ደግ ጊዜ ሲያጋጥማቸው የሚያሽቃብጡት ምዕራባውያን ሀገራት ለወያኔ የጀርባ አጥንት ሆነው ሲረዱት እንዳልነበር ዛሬ ሁሉንም ድርጊት በማወቃቸው እና ትዕዛዛቸውን አልቀበል ሲላቸው ጊዜ ጠብቀው የበቀል እርምጃ መውሰድ መጀመራቸው ለነመለስ ከፍተኛ ኪሳራ ብቻ ሳይሆን የኪሳራ ኪሳራ መሆኑን ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡